ቁጥር፦ ጓ1162/11/15383

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

**ለአክሱማይ ሚዲያ**

**መቐለ**

አክሱማይ ሚዲያ ለኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ በቁጥር አከ፡43፡ 2016 በቀን 28/11/2016ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የሚዲያው ስም በመቐለ ከተማ ከሚገኘው እና መጠሪያውን አክሱማይ ዋዕላ ከሚባል ፓርቲ ጋር የስም መመሳሰል ያለው መሆኑን በመጥቀስ ይህም በስራው ላይ ችግር የፈጠረበት በመሆኑ ቦርዱ ተገቢ የሆነ እርምጃ እንዲወስድ በማለት አመልክተዋል።

ቦርዱም የአክሱማይ ሚዲያን አቤቱታ ተቀብሎ ለአክሱማይ ዋዕላ ፓርቲ ምላሽ እንዲሰጥ በማለት አቤቱታውን አባሪ አድርጎ የላከ ሲሆን የአክሱማይ ዋዕላ ፓርቲውም በቁጥር አዋ/0095/15 በቀን 04/04/2017ዐዓ/ም በተጻፈ መልስ የኢትዮጲያ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁትር 1162/11 አንቀጽ 69/ለ/ መሰረት አንድ ፓርቲ የመረጠው ስም አህጽሮተ ስም አርማ ወይም የመለያ ምልክት በሌላ ፓርቲ የተያዘ ወይም ከሌላ ፓርቲ ስም አህጽሮተ ስም አርማ ወይም የመለያ ምልክት ጋር መራጮችን ሊያሳስት በሚችል ደረጃ የሚቀራረብ ከሆነ በሚል የተደነገገ በመሆኑ የአክሱማይ ሚዲያ ይህንን አቤቱታ ማቅረብ አይችልም በሚል ምላሽ ሰጥቷል።

ቦርዱም የአክሱማይ ሚዲያ አቤቱታን ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 አንጻር መርምሮታል። በዚህም መሰረት አዋጅ ቁጥር 1162/11 አንቀጽ 69 መመዝገብ ስለማይችል የፖለቲካ ፓርቲ በሚደነግገው የህጉ ክፍል ላይ አንድ ፓርቲ  የመረጠው ስም አህጽሮተ ስም አርማ ወይም የመለያ ምልክት በሌላ ፓርቲ የተያዘ ወይም ከሌላ ፓርቲ ስም አህጽሮተ ስም አርማ ወይም የመለያ ምልክት ጋር መራጮችን ሊያሳስት በሚችል ደረጃ የሚቀራረብ ከሆነ ስያሜውን ይዞ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ ለመመዝገብ የማይችል መሆኑን ነው።

በመሆኑም የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ በቁጥር1162/11 መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር ስልጣን መነሻነት ጉዳዩን ሲመረምር አክሱማይ ዋዕላ የሚለው ስያሜ ከሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ስያሜ ጋር እንዲሁም የፓርቲው አርማ ከሌላ ፓርቲ አርማ ጋር የሚመሳሰል ከሆነ እና መራጬን የሚያሳስት ከሆነ ብቻ ቦርዱ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው።

ለድምጽዎ የሚያምኑን

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር
@NEBEthiopia
ኢሜይል
contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

CamScanner

ይሁንና "አክሱምይ ሚዲያ" በሚዲያ ሥራ ላይ የተሰማራ ድርጅት በመሆኑ፤ የፖለቲካ ፓርቲው ይህን ሥያሜ ቢይዝ ይደናገራል/ይሳስታል ብሎ ቦርዱ ስለማያምን የቀረበውን ጥያቄ ቦርዱ ያልተቀበለው መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

**ከአክብሮት ሰላምታ ጋር**

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ayele Gete
የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ም/ሰብሳቢ
Deputy Chairperson National Electoral Board

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘርፍ

CamScanner